




የከተማ አስተዳደሩ ለዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ዕውቅናና ምስጋና ባበረከተበት ወቅት፡፡





የከንቲባ ፅ/ቤት የሱፐርቪዥን ቡድን በዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ተገኝቶ የስራ አፈጻጸም በገመገመበት ወቅት





የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀሙን ከአጠቃላይ ሰራተኛው ጋር በተወያየበት ወቅት



በመዲናዋ ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ደማቅ ተቋማዊ አሻራ እያኖረ የሚገኘው የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በዛሬው ዕለት በይፋ የተመረቀውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሁለገብ ሕንፃ ግንባታ በአጭር ጊዜ እና በላቀ ጥራት አከናውኖ ለአገልግሎት በማሰናዳቱ ከከተማ አስተዳደሩ ዕውቅናና ምስጋና ተችሮታል። ፕሮጀክቱ በዚህ ደረጃ ዕውን እንዲሆን ሌት ተቀን የተጋችሁ የቢሮው አመራርና ሰራተኞች ክብር ይገባችኋል

## እንኳን ደስ ያላችሁ/እንኳን ደስ ያለን!!!!

SUBSCRIBE

LIKE & SHARE

## የላፍቶ ቁጥር 2 ሁለገብ የገበያ ማዕከል ተጠናቆ በይፋ በተመረቀበት ወቅት ።





መዲናዋን ነዋሪዎች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡና ከሕብረተሰቡ ፍላጎቶች የተቀዱ ፕሮጀክቶችን በላቀ ጥራትና ዘመንን በተረዱ የምህንድስና ዕሳቤዎች በማከናወን በስፋት ለአገልግሎት እያበቃ የሚገኘው የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ልዩ ቦታው ኃይሌ ጋርመንት እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ሲያስገነባው የቆየውን የላፍቶ ቁጥር 2 ሁለገብ የገበያ ማዕከል ግንባታን አጠናቆ በዛሬው ዕለት የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ እና የኢፌዴሪ ንግድ እና ቀጠናዊ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር ካሳሁን ጎፌ እንዲሁም ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች በተገኙበት በይፋ አስመርቋል። በአጠቃላይ በ88 ሺህ ካ.ሜ ቦታ ላይ በተገነባው በዚህ ዘመናዊ የገበያ ማዕከል ውስጥ ከተካተቱ ግንባታዎች ውስጥ 3,700 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈና ለባንክ ፣ ለቢሮ ፣ ለካፊቴሪያና ሬስቶራንት አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎችን ጨምሮ የመሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲሁም ከምድር በታች በሚገኘው የህንፃው አካል ላይ የተዘጋጀ የእህል መካዘን የያዘ ባለ 4 ወለል ሕንፃ ይገኝበታል።ሌላኛው የዚህ ፕሮጀክት አካል የሆነውና በ1,700 ካ.ሜ ላይ ተገንብቶ እያንዳንዳቸው 70 ካ.ሜ ስፋት ያላቸው 6 ማቀዝቀዣ ክፍሎች ፣ መካዘኖች እና ቢሮዎች የተካተቱበት ባለ 3 ወለል የሱፐርማርኬት ሕንፃ ይጠቀሳል።

እያንዳንዳቸው 40 ካ.ሜ ስፋት ያላቸው 144 የተናጠል ሱቆችን የያዙ 9 የግብርና ግብዓቶች ጅምላ ማከፋፈያ ብሎኮች ሌሎቹ በፕሮጀክቱ የተካተቱ ግንባታዎች ሲሆኑ ከነዚህ በተጨማሪም እያንዳንዳቸው በ1,500 ካ.ሜ ላይ የተገነቡ 2 የጥራጥሬና የእህል መጋዘኖችም ተሟልተውለታል።

ከዚህ... በተጨማሪ የገበያ ማዕከሉ እንዲሰጥ የታሰበውን ዘመናዊና የተደራጀ አገልግሎት ያግዛሉ የተባሉ 2.9 ኪ.ሜ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ ፣ ዘመናዊ የአትክልት ማጠቢያ ፣ 150 ኪዩቢክ ሜትር የመጠጥ እንዲሁም 300 ኪዩቢክ ሜትር ለእሳት አደጋ መከላከያ የሚያገለግል ውሀ የሚይዙ የጂ.አር.ፒ. ውሀ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ፣ የጀነሬተርና የፓምፕ ክፍሎች ፣ 40 የቆሻሻ ማስወገጃ ገንዳዎች ፣ እያንዳንዳቸው 10 ክፍሎች ያሏቸው 9 መፀዳጃ ቤቶች እንዲሁም የአረንጓዴ ስፍራዎች ተሟልተውለታል። የዚህ ፕሮጀክት ዕውን መሆን አምራቹንና ሸማቹን ያለ አንዳች የደላላ ጣልቃ ገብነት በቀጥታ በማገናኘት አስተዳደሩ የሕብረተሰቡን የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የአዝዕርትና የሰብል ግብዓቶች ፍላጎት ለመመለስ የሚደረገውን ጥረት በዕጅጉ ከማገዙም ባሻገር በመዲናዋ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መስተጋብሮች ላይ የራሱን አዎንታዊ ሚና እንደሚጫወት ይጠበቃል። ቢሮው የዚህን ማዕከል የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታ በዋነኝነት በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት በአካላዊ ጥግግት የሚከሰተውን የህብረተሰቡን ተጋላጭነት ለመቀነስ ታስቦ በፒያሳ አካባቢ የነበረውን የተጨናነቀ የአትክልት መሸጫ ስፍራ ወደተሻለ ከባቢ ለማዛወር በተሰራው ስራ በአንድ ወር ገደማ ስራውን አጠናቆ ለአገልግሎት ማብቃቱ የሚታወስ ነው።

# በበጀት ዓመቱ በቢሮው የተከናወኑ የመንግስትና የፓርቲ ተግባራት አመርቂ ውጤት የታየባቸው መሆናቸው ተመላከተ።





በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ፅ/ቤት የተዋቀረው የሱፐርቪዥን ቡድን በዛሬው ዕለት በከተማው ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ተገኝቶ የበጀት ዓመቱን የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች አፈፃፀም ገምግሟል። የሱፐርቪዥን ቡድኑ በቢሮው በነበረው ምልከታ በተለይ ከፕሮጀክት አፈፃፀም ፤ ከአገልግሎት አሰጣጥ ፤ ከቴክኖሎጂ ትግበራ ፤ ምቹ የስራ ከባቢን ከመፍጠር እንዲሁም ከፓርቲ ስራዎች አፈፃፀም አንፃር የተቋሙን ቁመና ገምግሟል። በዚሁ መድረክ ላይ ለቡድኑ ማብራሪያ የሰጡት የቢሮው ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም እንዳሉት በጊዜ ማዕቀፉ በቢሮው መደበኛ እና ከመደበኛ ዕቅድ ውጪ በተከናወኑ ተግባራት ላይ የተመዘገቡት አመርቂ ውጤቶች በተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እመርታ እያሳየ የመጣው የማስፈፀምና የመፈፀም ዓቅም የደረሰበትን የላቀ ከፍታ የሚያሳዩ ተጨባጭ አስረጂዎች ናቸው ብለዋል።

ኃላፊዋ አያይዘውም ቢሮው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ እያሳደረ ለሚገኘው በጎ ተፅዕኖ ዓቅም ይሆናሉ ያላቸውን ከዘመን ጋር የተራመዱ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስርዓቶችን ፤ አገልግሎቱን ከእጅ ንክኪ የፀዳ ለማድረግ የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችን ፤ ወጪ እና ጊዜን የሚቆጥቡ አማራጭ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን እና መሰል ተግባራትን ዕውን አድርጎ ባከናወናቸው ስራዎች ፍሬያማ ውጤት ማግኘቱን በማሳያ አስረድተዋል።





የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
lis Ababa Design & Construction Works Burea

SUBSCRIBE

LIKE & SHARE

## ቢሮው በበጀት ዓመቱ በማዕከልና በክፍለከተማ መዋቅሮቹ 431 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ አቅዶ 700 ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ለአገልግሎት አብቅቷል።





**"በጀት ዓመቱ ያቀድናቸውን አጠቃላይ ስትራቴጂክ ግቦች በሙሉ በላቀ አፈፃፀም ያሳካንበት ፍሬያማ ጊዜ ነው" ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም ( የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ )**



የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀሙን ከአጠቃላይ ሰራተኛው ጋር በዛሬው ዕለት ገምግሟል። መድረኩን የመሩት የቢሮው ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም ለሰራተኛው ባስተላለፉት መልዕክት እንደ ቢሮ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ያቀድናቸውን ስትራቴጂክ ዕቅዶቻችንን ሙሉ በሙሉ በከፍተኛ አፈፃፀም አሳክተናል ያሉ ሲሆን ለዚህ አመርቂ ውጤትም ታላቅ አበርክቶ ያኖሩትንና በእርሳቸው አገላለፅ "የውጤቱ ባለቤት" ብለው የጠሯቸውን የተቋሙን አጠቃላይ አመራርና ሰራተኞች አመስግነዋል። ኃላፊዋ በዚሁ ንግግራቸው ቢሮው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ወደ ከፍታ የሚያመጡና ከዘመን የተናበቡ እንዲሁም መጪውን ጊዜ ያማተሩ የቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በተቋማችን ዕውን ለማድረግ የሄድንበት ርቀት አመርቂ ፍሬ ያየንበት ነው ያሉ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ውስን የሆነውን የሕዝብ ኃብት በአግባቡ ለመጠቀም ዓቅም እየሆነ የመጣውንና ቀላል የማይባል ኃብትን ለመንግስት እያስቀረ የሚገኘውን የግንባታ ክፍያ ድርድር ስርዓትን የፍትሀዊነትና የተገቢነት መርሆዎችን ተከትሎ በላቀ ሙያዊ ስነ-ምግባርና በትውልድ ኃላፊነት ስሜት በመምራት ያስመዘገብነው ተጨባጭ ውጤት ሌላኛው የበጀት ዓመቱ ደማቅ ስኬታችን ነው ብለዋል። በጊዜ ማዕቀፉ ሕዝብ የጣለብንን ተልዕኮ በብቃት ከመፈፀምና ከማስፈፀም በተጓዳኝ በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎች ፤ በሰው ተኮር ስራዎቻችን እንዲሁም በሌሎች የመዲናዋ ሁለንተናዊ የልማት ክንውኖች ላይ ያሳረፍነው ተቋማዊ አሻራ ቀላል የማይባል ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊዋ እነኚህ ሁሉ ተግባራት የታለመላቸውን ግብ ይመቱ ዘንድ የተመሩባቸው መርሆዎች ፤ የተዘረጋው ወጥነት ያለው የድጋፍና ክትትል ስርዓት ፤ ግብን መሰረት አድርገው የተፈፀሙ ተቋማዊ ቅንጅቶችና ትስስሮች ፤ በቢሮው በተጨባጭ የተስተዋለው የዳበረ የስራ ባህል ፤ የአመራሩና የሰራተኛው የማስፈፀም ዓቅም መጎልበት ፤ የከተማው ከፍተኛ አመራር ያላሰለሰ ድጋፍና ክትትል እና መሰል አስቻይ ሁኔታዎች የላቀ ድርሻ እንደነበራቸው ጠቁመዋል።





# ቢሮው የ260 ሺህ ብር ቦንድ ግዥ መፈጸሙን ገልጻል።



"በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ ድርሻውን እየተወጣ የሚገኘው ቢሮው በመጪው መስከረም በይፋ እንደሚመረቅ በተበሰረው የህዳሴ ግድብ ላይ ተቋማዊ አሻራችንን ለማኖር ዕድሉን በማግኘታችን ክብር ይሰማናል"

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በመጪው መስከረም በይፋ እንደሚመረቅ ክቡር ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ በዛሬው የፓርላማ ውሏቸው ማብሰራቸውን ተከትሎ የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም መልዕክት አስተላልፈዋል።

የህዳሴ ግድብ "ፕሮጀክት" ብቻ ብለን የምናልፈው ክንውን ሳይሆን የሁለንተናዊ ብልፅግናችን ካስማ ማረፊያ እና የታላቁ ሀገራዊ ትልማችን መወጣጫ እርካብም ጭምር ነው ያሉት ኃላፊዋ በዚህ የትውልዱ ቃልኪዳን እና የዘመናችን ታላቅ ክስተት በሆነው ተግባር ላይ ተከታታይነት ባለው መልኩ ሀብት በማሰባሰብ አሻራችንን ለማኖር ዕድል በማግኘታችን እንደተቋም ክብር ይሰማናል ብለዋል።

ኃላፊዋ አያይዘውም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሀብት ማሰባሰብ ንቅናቄ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተከታታይነት በስጦታና በቦንድ ግዢ ለተሳተፉ የቢሮው አመራርና ሰራተኞች እንዲሁም የዘርፉ ተዋንያን ምስጋናቸውን አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ባለፉት 6 ወራት ብቻ ባደረገው ንቅናቄ ከዘርፉ ተዋንያን 339 ሺህ ብር በስጦታ እና 10 ሺህ ብር በቦንድ ግዢ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ሰራተኛው ከወር ደመወዙ በመቀነስ የ 260 ሺህ ብር ቦንድ ግዢ ፈፅሟል።

ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም
የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ

# በቢሮው የበጎ ፍቃድ ፕሮግራም የተገነቡ የዓቅመ ደካማ ቤቶች ለነዋሪዎች ተላለፉ።





አዲስ አበባ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ በ2017 የበጎ ፍቃድ ፕሮግራሙ ባለሀብቶችን በማስተባበር በአዲስ ከተማ ክፍለከተማ ወረዳ 05 ሲያስገነባቸው የቆየውን የ14 እማወራና አባወራ ቤቶች አጠናቆ በይፋ ለነዋሪዎቹ አስረክቧል። የቤቶቹን ቁልፍ ለነዋሪዎች ያስረከቡት የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ ክብርት ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም በስነ-ስርዓቱ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ቢሮው በዓዋጅ ተቆጥሮ ከተሰጠው ተግባራት በተጨማሪ ማሕበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ ጠቅሰው ለዚህም ማሳያ የዛሬዎቹን 14 ቤቶች ጨምሮ ከወር በፊት በጉለሌ ክፍለከተማ ወረዳ 08 ተገንብተው ለተጠቃሚዎች የተላለፉትን 16 የዓቅመ ደካማ ቤቶችን በአብነት አንስተዋል። ኃላፊዋ አያይዘውም የቢሮውን ማሕበራዊ ጥሪ በቀና ልብ ተቀብለው ካፈሩት ጥሪት ውስጥ በጎ አሻራቸውን በትውልድ ላይ ላኖሩት ኢ/ር ዳዊት እምሩ እንዲሁም ኢ/ር ዮሴፍ አበበ ያላቸውን ምስጋና በቢሮውና በነዋሪዎቹ ስም አስተላልፈዋል። በዛሬው ዕለት ከተላለፉት ቤቶች ውስጥ የ 9 እማወራና አባወራ ቤቶችን አፍርሶ በአዲስ እና ዘመናዊ መልኩ ገንብቶ ያጠናቀቀው የዳዊት እምሩ ሕ/ስ/ተቋራጭ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ ኢ/ር ዳዊት እምሩ በርክክቡ ወቅት እንዳሉት ለሀገር ውለታ የዋሉ ወገኖችን ዓቅም በፈቀደ መልኩ ለማገዝ ዕድሉን ማግኘት በራሱ ልባዊ ደስታን የሚያጭር ብቻም ሳይሆን ፍፁም መንፈሳዊ ዕርካታንም የሚያቀዳጅ ተግባር ነው ያሉ ሲሆን እንደ ዜጋ በዚህ መልካም ስራ ላይ አሻራቸውን ማኖራቸው እንዳስደሰታቸው ጠቀሰዋል። ቢሮው በዚህ በጀት ዓመት በማዕከል ደረጃ 30 እንዲሁም በክፍለከተማ መዋቅሩ 66 በአጠቃላይ 96 የዓቅመ ደካማ ቤቶችን በማደስ ለነዋሪዎቹ አስተላልፏል።





# የቢሮው አገልግሎት አሰጣጥ አበረታች እመርታ እያሳየ እንደሚገኝ ተገለፀ።





የከተማውን አስፈፃሚ ተቋማትን የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት በተሻለ መልኩ ለመገንባት እየሰራ ያለው የአዲስ አበባ ፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን በዛሬው ዕለት በአዲስ አበባ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ተገኝቶ ድጋፍና ክትትል አድርጓል። ቡደኑ በስትራቲጂካዊ ግቦች አፈጻጸም ፣ በመልካም አስተዳደርና በአገልግሎት አሰጣጥ፤ በሌብነትና ብልሹ አሰራር የተሻለ የፕሮጀክት አፈጻጸም በአቅም ግንባታ የታገዘ ስለመሆኑ ፤ በግንባታውን ዘርፍ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ስለተሰሩ ስራዎች እና ቢሮው ከሌሎች ተቋማት ጋር ስላለው ቅንጅታዊ አሰራር በድጋፍና ክትትሉላይ የተነሱ ዋና ዋነ ነጥቦች ነበሩ ። በአጠቃላይ በድጋፍና ክትትሉ የቢሮው የአገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እመርታ እያሳየ እንደሚገኝ ቡድኑ ካደረገው ምልከታ መገንዘቡ ተገልጿል ።





የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
lis Ababa Design & Construction Works Burea



# ባለ 13 ወለሉ የሲኒማ ኮምፕሌክስ 4B+G+8 ሕንፃ ለይፋዊ ምርቃት እየተሰናዳ ይገኛል።




የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በበጀት ዓመቱ አጠናቆ ለአገልግሎት ለማብቃት ካቀዳቸው ዘርፈ ብዙ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የሆነውና በልደታ ክ/ከተማ ልዩ ቦታው ሰንጋተራ አካባቢ በ2,473 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ያስገነባው ዘመናዊው የሲኒማ ኮምፕሌክስ ሕንፃ ለይፋዊ ምርቃት እየተዘጋጀ ነው።ከአንድ ክፍለዘመን በላይ እንዳስቆጠረ የሚነገርለት የኢትዮጵያ ዘመናዊ የፊልም ኢንዱስትሪ ከተጓዘው ዕድሜ አንፃር ዛሬ ላይ የደረሰበት የዝማኔ ደረጃ ኢንዱስትሪው በዓለም ዓቀፍ መድረክ ካለበት ቁመና እጅጉን የራቀ እንደሆነ በግልፅ ይስተዋላል። ይህን የተረዳው የከተማ አስተዳደሩ መዲናዋ እየተጓዘችበት ከምትገኘው የዘመናዊነት ግስጋሴ ጋር የተናበበና ዓለም-ዓቀፋዊ ደረጃን ያገናዘበ ዘመናዊ የሲኒማ ማዕከል ገንብቶ እንሆ ለአገልግሎት ለማዋል እየሰራ ይገኛል። 3 ብሎኮች ባሉት በዚህ ሕንፃ ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖጂ የሚታገዙ የድምፅ ፣ የዳታና የቬንትሌሽን ስርዓቶች የተዘረጉላቸው 2 ሲኒማዎች የተካተቱ ሲሆን 974 የተመልካች ወንበሮችና 60 ካሬ ስክሪን የተገጠመለት የአዋቂዎች ሲኒማን ጨምሮ 800 የተመልካች ወንበሮችና 50 ካሬ ስክሪን የተገጠመለት የህፃናት ሲኒማዎች ዕውን ተደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ የሲኒማቶግራፊ ጥናት ማዕከላት ፣ ስቱዲዮዎች ፣ የጉዞ ኤጀንቶችና የገንዘብ ምንዛሪና የአስተዳደር ቢሮዎችን ጨምሮ በአንድ ጊዜ ከ150 በላይ ተሽከርካሪዎችን የሚያስተናገድ ዘመናዊ ፓርኪንግም 4 ወለሎች ባሉት የሕንፃው የቤዝመንት ውስጥ ተሰናድቷል።



በፕሮጀክቱ ባማኮን ኮንስትራክሽን በስራ ተቋራጭነት እንዲሁም ኖብል ኮንሰልቲንግ በአማካሪነት ተሳትፈውበታል።



የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
dis Ababa Design & Construction Works Burea

SUBSCRIBE

# ጥምር አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ታስቦ እየተከናወነ የሚገኘው ግዙፉ የሀያ ሁለት ፓርኪንግ ፣ ፕላዛ እና ሞል ግንባታ እየተፋጠነ ይገኛል።

የመዲናዋን ገፅታ ከመሰረቱ የሚቀይሩና ለዓለም-ዓቀፋዊነት ከፍታዋ መሰረት የሚጥሉ ዘመናዊና ግዙፍ ግንባታዎችን በሁሉም ዘርፍ እያከናወነ የሚገኘው የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በበርካታ የከተማዋ ስፍራዎች የተሽከርካሪ ፍሰቱን የሚያሳልጡ ብቻም ሳይሆን ማራኪ ገፅታን የሚከስቱ ፓርኪንጎችና ፕላዛዎችን እያስገነባ ይገኛል። በዋነኝነት 3 የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሰጥ ታስቦ በመዲናዋ እምብርት ሀያሁለት ጎላጉል አካባቢ በ6,500 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተጀመረው ግዙፉ 2B+G+20 የፓርኪንግ ፣ ፕላዛ እና ሞል ግንባታ ከነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ ይጠቀሳል። በዚህ ፕሮጀክት ዕውን ከሚደረጉ አገልግሎቶች መካከል በሕንፃው 2 ቤዝመንቶች ውስጥ የሚተገበረውና በአንድ ጊዜ ከ200 በላይ ተሽከርካሪዎች ማስቆምና ከ40 በላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ቻርጅ ማድረግ የሚያስችሉ ፋሲሊቲዎች የሚሟሉለት የፕሮጀክቱ አካል አንዱ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በርካታ ሱቆች ፣ አምፊ ቴአትር ፣ ካፊቴሪያና የመዝናኛ ስፍራዎች ዕውን የሚደረጉበት ዘመናዊ ፕላዛ ሌላኛው የሚጠበቅ የፕሮጀክቱ አካል ነው። 20 ወለሎች የሚኖሩትና በቀጣይ በመንግስትና በግል አጋርነት (PPP) ሞዳሊቲ እንዲለማ ውጥን የተያዘለት ዘመናዊ ሞል ደግሞ ሶስተኛው የፕሮጀክቱ አካል ሲሆን ቢሮው ይህን ጥምር ፋይዳ ያለውን ፕሮጀክት በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ አጠናቆ ለታለመለት ዓላማ ለማሰናዳት ትኩረት ሰጥቶ እያከናወነው ይገኛል። በዚህ ፕሮጀክት ኢምፕረሽን ኮንስትራክሽን በስራ ተቋራጭነት እንዲሁም ቹዝን ኮንሰልቲንግ በአማካሪነት እየተሳተፉበት ይገኛል።









SUBSCRIBE

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
lis Ababa Design & Construction Works Burea